ቁጥር ናክመክ 126/2013

ቀን 27/07/2013 ዓ.ም

ለ_______________________________________________________መሠረተ ክርስቶስ አጥቢያ

የእግዚአብሔር ምህረትና ቸርነት ይብዛላችሁ

ጉዳዩ፡- የኮቪድ 19 ወቅታዊ ሁኔታን በተመለከተ ሊደረጉ የሚገባቸዉ ጥንቃቄዎችን ስለማሳሰብ

የናዝሬት ክልል መሠረተ ክርስቶስ የክልሉ አስተዳደር መሪዎች ጉባኤ በመጋቢት 25/2013 ዓ.ም ባካሄደዉ ስብሰባ በወቅቱ ያለዉን የአገራችንን የኮቪድ 19 ሥርጭት አሁን ያለበትን ሁኔታና ከመንግስት እየተሰጠ ያለዉን ማስጠንቀቅያ እና ብዙዎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች ፣ መዕመናን በዚህ ህመም በመጠቃት እየሞቱ ፣ እየተቸገሩ እንዳሉ ፣ ሥርጭቱም በከፍተኛ ሁኔታ እየተዛመተ እንዳለ በስፋት በመመልከት ከዚህ በታች ያሉትን ጥንቃቄዎች እንዲደረጉ እናሳስባለን

1 . መንግሥት ያወጣዉን ፕሮቶኮል መሠረት ያለዉ አገልግሎት መስጠት

- እጅን መታጠብ ወይም ሳንታይዝ ማድረግ
- ርቀትን መጠበቅ
- ማስክ ማድረግ
- የምንገለገልባቸዉን ጸሎት ቤት ፣ ማሥተማሪያ ክፍሎች ፣ ቢሮዎች ፣ ወንበሮች ፣ ወዘተ የማጽዳት ሥራ መሥራት

2 . ተጎዳኝ ህመም ያለባቸዉና ተጋላጭ የሚሆኑ ወገኖች በከፍተኛ ጥንቃቄ ማገልገልና መገልገል እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት

3 . ከማይክ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲደረግ ካልተቻለ በድምጽ ብቻ የሚገለገልበትን ሁኔታ ማመቻቸት

4 . ኪቦርድና ድምጽ መሣሪያ አከባቢ በጥንቃቄ እንዲሠራ አንድ ሰዉ የሚሠራበትን ሁኔታ ቢመቻች

5 . ኮንፍራንሶች ፣ መነቃቂያዎች ፣ ልዩ ፕሮግራሞች ፣ ሪትሪት/የጋራ ጉብኝቶች ፣ ሁኔታዎች እስኪስተካከሉ ቢቆሙ

6 . በጸሎት ቤት ግቢና አከባቢ ሁሉ ጥንቃቄ እንዲደረግ የሚያመለክት ጽሑፍ ቢለጠፍ

7 . ጥበቃዎችና ዲያቆናት በቁጥር አንድ የተጠቀሱትን ሃሳቦች ሳያሞሉ ወደ ጸሎት ቤት እንዳይገቡ ክትትል እንዲያደርጉ

8 . ድንገት በሽታዉ ከፋቶ ጸሎት ቤት ሊዘጋ ቢችልስ የሚል ቅድመ ዝግጅት ማድረጉ በጣም ወሳኝ ስለሆነ እስትራቴጂካል ፕላን የመቅረጽ ሥራ ቢሠራ

9 . እጅ በመጫን የሚደረጉ አገልግሎቶች ከተቻለ ባይደረጉ የግድ ከሆነ ግን በከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲደረግ

ከላይ የተጠቀሱትን ሀሳቦች እና አጥቢያዋ ያለዉን አዉዳዊ ሁኔታ በማየት አመቺ ሁኔታዎችን እንድታመቻቹ እያልን በተለይ የሽማግሌዎች ጉባኤና አገልጋዮች ፣ ዘርፎች ፣ ይህንን ሃላፊነት በአስቸኳይ ወደ ተግባራዊ እንዲያደርጉ እናሳስባለን ፡፡

ጌታ ይባርካችሁ